የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፲፯
አዲስ አበባ የካቲት ፳፭ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

27th Year No. 17
ADDIS ABABA, 4th March, 2021

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፴፭/፪ሺ፲፫

የኢትዮጵያ የምርጫ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነ ምግባር አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፷፪/፪ሺ፲፩ን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ.....ገጽ ፲፫ሺ፭

Content

Proclamation No.1235/2021

A proclamation to Amend the Ethiopian Electoral, Political Parties Registration and Election's Code of Conduct Proclamation No.1162/2019.....Page 13008

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፴፭/፪ሺ፲፫

የኢትዮጵያ የምርጫ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነ ምግባር አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፷፪/፪ሺ፲፩ን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ የምርጫ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነ ምግባር አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፷፪/፪ሺ፲፩ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ የምርጫ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነ ምግባር /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፷፪/፪ሺ፲፩ን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፴፭/፪ሺ፲፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

PROCLAMATION NO.1235/2021

A PROCLAMATION TO AMEND THE ETHIOPIAN ELECTORAL, POLITICAL PARTIES REGISTRATION AND ELECTION'S CODE OF CONDUCT PROCLAMATION NO.1162/2019

WHEREAS, it has become necessary to amend the Ethiopian Electoral, Political Parties Registration and Election's Code of Conduct Proclamation No.1162/2019;

NOW THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

1. Short title

This Proclamation may be cited as "The Ethiopian Electoral, Political Parties Registration and Election's Code of Conduct /Amendment/ Proclamation No.1235/2021 to amend Proclamation No.1162/2019."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፪. ማሻሻያ

፩/ ይህ የኢትዮጵያ የምርጫ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነ ምግባር አዋጅ ቁጥር ፩፻፩፱፱፬/፪፻፲፩ አንቀጽ ፴፩(፫) እና ፴፪(፪) ለጊዜው አገር አቀፍ ምርጫ ብቻ ተፈጻሚ እንዳይሆኑ ታግደው በሚተሉት አዲስ አንቀጾች ፴፩(፮) እና ፴፪(፰) ተተክተዋል፡

ሀ/ ፴፩(፮) በፍርድ ቤት ውሳኔ ወይም በአእምሮ ህመም ምክንያት ያልተገደቡ የምርጫ ክልሉ ነዋሪዎች ውስጥ ከሁለት ሺህ አምስት መቶ የማያንስ የድጋፍ ፊርማ ማቅረብ አለበት፡፡ ሆኖም የግል ዕጩ ተወዳዳሪው የአካል ጉዳተኛ ማቅረብ ያለበት የድጋፍ ፊርማ ብዛት ከአንድ ሺህ አምስት መቶ የማያንስ ይሆናል፡፡ ይህም ስድስተኛው አገር አቀፍ ምርጫ ላይ ብቻ ተፈጻሚ ይሆናል፡

ለ/ ፴፪(፰) በዓለም አቀፍ ደረጃም ሆነ በአገራችን የሥርጭት መጠኑ ያልተገታውን የኮቪድ ፲፱ ወረርሽኝ መከላከል መሠረት ባደረገ መንገድ ለስድስተኛው አገር አቀፍ ምርጫ ለመዘጋጀትና ምርጫውን ለማካሄድ ሲባል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትም ሆነ ለክልል ምክር ቤት በዕጩነት ለመቅረብ የተጠየቀው የድጋፍ ፊርማ በስድስተኛው አገር አቀፍ ምርጫ ላይ ብቻ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

2. Amendment

1/ Article 31(3) and 32(2) of The Ethiopian Electoral, Political Parties Registration and Election's code of Conduct Proclamation No. 1162/2019 are hereby suspended and replaced by the following new Articles 31(6) and 32(8) for the upcoming election only:

a) 31(6) An independent candidate shall secure the endorsement signature of not less than 2,500 signatures from the constituency's residents whose voting rights have not been restricted by law or a court decision or due to insanity. However, the endorsement signature for an independent candidate with physical disability shall not be less than 1,500. This will only be applicable for the sixth national election;

b) 32(8) in order to prepare for and conduct the sixth national election, as provided under Sub Article 2 of this Article, the number of endorsement signatures required for Candidates of Political parties for both the House of Peoples' Representatives and Regional Councils will not be applicable for the sixth national election. This is in consideration of the efforts to mitigate the spread of the Covid-19 pandemic, which has been spreading rapidly both nationally and internationally.

፫. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ከጥር ፳፭ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ፳፪ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም

ሳህለወርቅ ዘውዴ
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዝዳንት

3. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on its adoption by the House of Peoples' Representatives on the 2nd day of February, 2021.

Done at Addis Ababa, On this 1th Day of March, 2021

SAHLEWORK ZEWDE
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA